በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁላይ 11-20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከጁላይ 21-31/2024 እና ከኦገስት 1-10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ - 3 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 5 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት - 5 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር - 5 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 6 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 6 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ - 7 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ - 7 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 8 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 9 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን - 9 -
እ.ኤ.አ ኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ - 9 -
ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 10 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 11 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ - 12 -


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በጁላይ ሁለተኛው አሥር ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ተጠናክረው ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን የሸፈነ ዝናብ አግኝተዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘምበሰሜን አጋማሽ፣ መካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብና ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአዲስ አበባ ቦሌ 39.2 እና 44.0፤ በባህር ዳር 67.8. 38.5 እና 36.2፣ በኮምቦሎቻ 35.0፣ በደብረ ማርቆስ 36.0 እና 61.5፣ በቢሾፍቱ 35.5፣ በጅማ 37.8 እና 36.5፣ በመተህራ 36.8፣ በነቀምቴ 65.0 እና 36.8፣ በአይራ 46.8፣ 58.6 እና 53.2፣ በአለም ተፈሪ 31.2፣ በአማን 47.4 እና 58.8፣ በአምባ ማርያም 34.2፣ በአንገር ጉቲን 33.4፣ 35.2 እና 48.4፣ በአርጆ 38.8 እና 32.6፣ በአፅቢ 112.0፣ በአዋሽ አርባ 60.0፣ በቦሬ 31.6፣ በቻግኒ 32.8 እና 33.2፣ በጨፋ 44.2፣ በጭራ 55.5፣ በደብረ ብርሃን 47.8፣ በዳንግላ 43.3 እና 47.2፣ በደብረ ወርቅ 37.4፣ በደምቢ ዶሎ 32.8፣ በዳሊፋጊ 117.3፣ በእነዋሪ 36.6፣ በፊቼ 32.4፣ በፉኚዶ 30.8 እና 42.5፣ በጋምቤላ 46.2፣ በገለምሶ 32.5፣ በጊዳ አያና 46.1 እና 48.0፣ በጊምቢ 36.7፣ በጉንዶ መስከል 34፣ በሀረሪ 53.0፣ በሆሳዕና 35.8፣ በእምድብር 30.8 እና 37.1፣ በካቺሴ 56.6፣ በላይበር 34.1፣ በሊሙገነት 30፣ በማንኩሽ 35.5፣ በማሻ 30.6፣ በሞጣ 50.8 እና 36.9፣ በአዳማ 41.0፣ በሰመራ 47.0፣ በሶኮሩ 41.8፣ በሻውራ 43.8 እና 33.7፣ በሾላ ገበያ 40.7፣ በሸኖ 43.2፣ በቴፒ 31.2 እና 62.3፣ በባቱ 44.4፣ በባቢሌ 32.0 እንዲሁም በካራሚሌ 33.9 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፤ የመካከለኛው፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ ማዕከላዊ፣ የሰሜን እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ፤ ምስራቅ፣ ደቡብና እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግህምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ እንዲሁም የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል መዠንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ልዩ ዞን ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄሌም፣ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ፣ ኢሉባቡር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ እና ከፋ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ፣ የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የወላይታ፣ የጋሞ፤ የጌዲኦ፣ የባስኬቶና የደራሼ ዞን፤ የሲዳማ ክልል ዞን፤ ከሱማሌ ክልል የፋፋን ዞንና የሲቲ፣ የኤረር፣ እንዲሁም የጃራና የኖጎብ ሰሜናዊው ክፍል ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ፣ አውሲ እና ጋቢ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ30-264 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-8 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ የቡርጂ፣ የኮንሶ የአሪና የአማሮ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል፣ የባሌ ደቡባዊው ክፍል፣ ከሱማሌ ክልል የሊበንና የዳዋ ዞኖች ላይ ከ11-20 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ 3 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲወዳደር ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፤ የመካከለኛው፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ፣ ምስራቅ፣ ደቡብና እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግህምራ እንዲሁም ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል መዠንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄሌም፣ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ፣ ኢሉባቡር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ቦረና፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፤ ከአፋር ክልል ዞን 1፣ 2፣ 3፣ 4 እና 5፤ የሲዳማ ክልል ዞን፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የወላይታ፣ የጋሞ፣ የጌዲኦ፣ የባስኬቶ፣ የደራሼ ዞን፣ የቡርጂ፣ የኮንሶ የኤሊና የአማሮ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ፣ የምዕራብ ኦሞ፣ ዳውሮ እና ከፋ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሀረሪ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠንና ስርጭት አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ
የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ
ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ እና የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ ሰብሎች ለመዝራትና፣ አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከኤፕሪል ጀምሮ ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለተለያዩ ቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ አልፎ አልፎም ወደ ደቡብ፣ ሰሜን ምስራቅ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ተስፋፍቶ የነበረው እርጥበት በአካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ እንቅስቃሴ እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ ጥሩ አስተዋጽኦ የነበረው ከመሆኑም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በሰሜን አጋማሽ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብና በምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት የአረም መስፋፋት እና በሰብሎችና በእንስሳት ላይ ጉዳት ያስከተለ እንደነበር ከስፍራው የተሰበሰቡ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የገጸ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውኃ ሀብትን ከማሻሻል እንዲሁም ወደ ግድቦች እና የተለያዩ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከማጎልበት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው ሲሆን እንዲሁም እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውኃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት ከማስቻል አንጻረ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላ በኩል ከነበረው ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ለመዋቀስም ያህል በትግራይ (አጽቢ)፣ በአማራ ክልል (ዳንግላ)፣ በአፋር፣ በሀረር፣ በባቱ እና በጅማ አካባቢዎች ላይ የቅጽበታዊ ጎርፍ ክስተት የነበረ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ በንብረት እና በመሰረተ ልማት ላይ መጠነኛ ጉዳት አድርሷል። በተጨማሪም በአንዳንድ የከተማ አካባቢዎች ላይ የትራፊክ መጨናነቅ የተስተዋለ ሲሆን በባቱም ደግሞ በተሽከርካሪዎች ላይ መጠነኛ ጉዳት አስከትሏል(ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በጁላይ ሦስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተሻለ ሁኔታ ይጠናከራሉ፡፡ ስለሆነም በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ በመደበኛው ሁኔታ ተጠናክሮ ይጥላል፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች የተጠናከረና የተስፋፋ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚኖረው ተከታታይነት ያለው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ቅጽበታዊ ጎረፍ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋህግምራ፣ አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፤ ማዕከላዊ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዌ፤ አሶሳ፤ ካማሺ ዞኖች እና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣ አኝዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ዞኖች፣ ጠምባሮ፣ ቀቤና እና ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድኦ፣ ባስኬቶ እና አማሮ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ፣ በደቡብና በምስራቅ ትግራይ፤ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ሸዋ፤ አብዛኛው አፋር፤ ጋምቤላ፤ መተከል እና በጎንደር ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በሌላ በኩል ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የባሌ እና ምስራቅ ባሌ ሰሜናዊው ክፍል፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀራር፣ ኤረር እና ኖጎብ፣ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ጋቢ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንሶ፣ አሪ ደራሼ እና ቡረጂ ዞኖች እንዲሁም ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 21-31, 2024
የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


## እ.ኤ.አ ኦገስት 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በይበልጥ የሚጠናከሩ ሲሆን የዝናቡ ስርጭትም በተሻላ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ላይ ከፍተኛ ጥንካሬ የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም በመጪዎቹ የኦገስት የመጀመሪያው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በተስፋፋ ሁኔታ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ሰሜን ምስራቅና እና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸው


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች የተነሳ በተለይም በሰሜንና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8 )፡፡

Rainfall performance (mm) for 1-10 Aug 2024




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የመኸር አምራችና የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸዉ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለግብርናው ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉና አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የሚገኘዉ እርጥበት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የመኸር ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን እንደሚያሻሽልና የመኸር ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና በአሁኑ ጊዜ እርጥበት በማግኘት ላይ ለሚገኙት በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላም በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ሰለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ የማደበሪያና ጸረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀም የዝናቡን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማከናዎን ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ እና የመሬት መንሸራተት መከሰት በተለይም በተከታታይ ዝናብ እያገኙ ባሉ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የጁላይ የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃን ከማሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች የውኃ አቅም ከማጎልበት አንጻር ጥሩ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ሊኖር ከሚችለው ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ እንዲሁም የወንዝ ዳርቻዎች ዉሃ ሙላት ክስተቶች በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በከተሞች አካባቢዎች ላይ ተጽዕኖ እንዳያጋጥም ከወዲሁ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡


ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et